«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

«በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» (ፊልጵስዩስ 2፡9-11)።



ልብ በል፡- መሢሑ ኢየሱስን አዳኝህና ጌታህ እንደሆነ ትቀበለውና ታከብረው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። መሢሑን ኢየሱስን እንደ አዳኝህ በተቀበልህ ጊዜ ለኃጢአቶችህ ሁሉ ይቅርታን ታገኛለህ። እግዚአብሔርም ሰማያዊ አባትህ መሆኑን ታውቃለህ። መንግሥተ ሰማይም ትገባ ዘንድ ዋስትና ይኖርሃል። መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህ ለመቀበል ፈቃድህ ከሆነ የሚከተለውን ጸሎት መጸለይ ትችላለህ። እግዚአብሔርም ጸሎትህን ይሰማል።

ኃያሉ እግዚአብሔር ሆይ፥ አገልጋይህ የሆነውን መሢሑ ኢየሱስን ወደ ዓለም ስለላክህ አመሰግንሃለሁ። እንደምትወደኝም በአገልጋይህ በኩል ስላሳየኸኝ አመሰግንሃለሁ። ከኃጢአቴም ይቅርታን አገኝ ዘንድ፥ በመስቀል ሊሰቃይና ሊሞት ስለላክኸው አገልጋይህ አመሰግንሃለሁ። የዘለዓለም ሕይወት ይኖረኝ ዘንድም አገልጋይህ የሆነውን መሢሑ ኢየሱስን ከሞት ስላስነሣኸው አመሰግንሃለሁ። ኃጢአተኛ ነኝና ኃጢአቴን ይቅር ትለኝ ዘንድ እጠይቅሃለሁ። ባሪያህ በሆነው በኢየሱስ ሞት ምክንያት የተገኘውን የኃጢአት ይቅርታ አሁኑኑ እቀበላለሁ። መሢሑ ኢየሱስም ጌታዬ ይሆን ዘንድ ጽኑ ፍላጎቴ ነው። ኢየሱስ የሚወዳቸውን ያህል ሌሎችን እወድ ዘንድ እርዳታህ አይለየኝ። ከኃጢአቴም አንጽተህ እኔን በመቀበልህ አመሰግንሃለሁ። ይህንንም ሁሉ ጌታዬና መድኃኒቴ በሆነው በመሢሑ በኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ፤ አሜን።